# ዕድሜያቸው ከ21 ዓመት በታች የሆኑ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ያለባቸውን ልጆች ለይቶ ማወቅ

የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ላለባቸው ግለሰቦች የትምህርት ሕግ (IDEA) መሠረት፣ የሜሪላንድ ስቴት **ለቤተሰቦች ያለምንም ክፍያ በማያመጣ ሁኔታ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ያለባቸውን ልጆች ለማግኘት፣ ለይቶ ለማወቅና ለመገምገም** ሙከራ ያደርጋል።

**ዕድሜያቸው እስከ 3 ዓመት** የሆኑ ሕጻናቶችን ማግኘት፣ ለይቶ ማወቅና መገምገም በእያንዳንዱ የሜሪላንድ አውራጃ ውስጥ የሚገኙት የሕጻናትና የልጆች መርሃ ግብር ኃላፊነት ነው። የእድገት መዘግየት ወይም የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ያለባቸው ሕጻናትና ልጆች **አስቀድሞ ችግር መፍቻ አገልግሎቶች** ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ አገልግሎቶች የተዘጋጁት አንድ ልጅ ለእድገት ያለውን ዕድል ለማበረታታትና ቤተሰቦች ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸውን ልጆች ተገቢውን ትኩረት እንዲሰጡ የሚያስችል ነው።

ዕድሜያቸው **ከ 3 ዓመት እስከ 21 ዓመት** የሆኑ ልጆችን ማግኘት፣ ለይቶ ማወቅና መገምገም በእያንዳንዱ የሜሪላንድ አውራጃ ውስጥ የሚገኘው የአካባቢው የትምህርት ሥርዓት ኃላፊነት ነው። በዚህ ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ያለባቸው ልጆች **ልዩ ትምህርት** እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ (ለምሳሌ የአነጋገር ሕክምና፣ የሰውነት እንቅስቃሴ ሕክምና፣ የሥራ ጉዳት ሕክምና)።

ሜሪላንድ ውስጥ አስቀድሞ ችግር መፍቻና ልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን በተመለከተ በይበልጥ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይደውሉልን፡
1-800-535-0182

# ዕድሜያቸው እስከ 21 ዓመት የሆኑ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ያለባቸው ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች የድጋፍ አገልግሎቶች

ዕድሜያቸው እስከ 21 ዓመት የሆኑ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ያለባቸው ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች፣ ሜሪላንድ በየአውራጃው የቤተሰብ ድጋፍ አገልግሎቶች አስተባባሪዎች አሉት። የቤተሰብ ድጋፍ አገልግሎቶች ዝርዝር ማውጫ በሚከተለው ድህረ ገጽ ይገኛል www.mdecgateway.org። የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ያለባቸውን ልጆች ለይቶ ስለማወቅ ተጨማሪ እርዳታ ወይም መረጃ ከፈለጉ እባክዎን ይደውሉልን።

Maryland State Department of Education
Division of Special Education/
Early Intervention Services
Family Services and Interagency Branch
200 West Baltimore Street, 9th floor
Baltimore, Maryland 21201
የነጻ ስልክ 1-800-535-0182
ፋክስ 410-333-8165

**Nancy S. Grasmick**
የስቴት ትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ

**James H. DeGraffenreidt, Jr.**
የስቴቱ ትምህርት ቦርድ ሊቀመንበር

**Carol Ann Heath**
ረዳት ስቴት ተቆጣጣሪ
የልዩ ትምህርት ክፍል/አስቀድሞ ችግር መፍቻ አገልግሎቶች

**Martin O'Malley**፣ አገረ ገዢ

Maryland State Department of Education
Achievement Matters Most

07/09

የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ ሥራ ቅጥርን ወይም በአንዳንድ የመርሀ-ግብር ተሳትፎዎችን በተመለከተ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል በጎሳ፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በዕድሜ፣ በብሄር፣ በሃይማኖት ወይም በአካል ጉዳት ላይ የተመሠረተ ምንም ዓይነት አድሎ አያደርግም። የመምሪያውን አመራር በተመለከተ ጥያቄዎች ካልዎት የእኩልነት ማረጋገጫና መፈጸሚያ ቅርንጫፋን በስልክ ቁጥር 410-767-0431, በፋክስ 410-333-2226 ወይም መስማት ለሚሳናቸው በ 410-333-6442 ይገናኙ። ይህ ሰነድ ተዘጋጀው በልዩ ትምህርት ክፍል/አስቀድሞ ችግር መፍቻ አገልግሎቶች ሲሆን፣ ከዩ.ኤስ. የትምህርት መምሪያ የልዩ ትምህርትና ማገገሚያ አገልግሎቶች፣ IDEA, ክፍል B፣ ችሮታ ቁጥር H027A080035A በተገኘ ገንዘብ ነው። እዚህ ውስጥ የተገለጹት አመለካከቶች በግድ የዩ.ኤስ. የትምህርት መምሪያ ወይም የማንኛውም ሌላ የፌዴራል ድርጅትን የሚያንጸባርቁ ስላልሆኑ እንደዛ መታየት የለባቸውም። መረጃው ከሕትመት ሕግ (ኮፒራይት) ነጻ ነው። አንባቢዎች አባዝተው መጋራት ይችላሉ ሆኖም እባካችሁ ከሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ፣ የልዩ ትምህርት ክፍል/አስቀድሞ ችግር መፍቻ አገልግሎቶች የመጣ መሆኑን አስታውቁ። በአካል ወይም አእምሮ ጉዳት ያለባቸው አሜሪካኖች ሕግ (ADA) መሠረት፣ በተጠየቀ ጊዜ ይህ ሰነድ በተለያዩ መልኮች ሊቀርብ ይችላል። የቤተሰብ አገልግሎቶችና የድርጅቶች ቅርንጫፍን በስልክ ቁጥር 410-767-0858 ወይም በፋክስ 410-333-1571 ይገናኙ።

# ልጅዎ የሚያይበት፣ የሚያዳምጥበት፣ የሚንቀሳቀስበት፣ የሚጫወትበት፣ የሚያወራበት፣ የሚማርበት ወይም የአኳኋኑ ሁኔታ ያሳስብዎታል?



- ልጅዎ የአካል ጉዳት ወይም የእድገት መዘግየት አለው ብለው ከ ጠረጠሩ **ዕድሜያቸው ከ21 በታች የሆኑ** ልጆችዎ ለምርመራ እና ለግምገማ ብቃት እንዳላቸው ያውቁ ነበር?

**ይደውሉልን!**
**1-800-535-0182**



የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ
የልዩ ትምህርት ክፍል/አስቀድሞ ችግር መፍቻ አገልግሎቶች

# አንድን ልጅ ለምርመራ እና ግምገማ መጠቀም



አንድ ልጅ የእድገት መዘግየት ወይም የአካል ጉዳት አለበት ብሎ የጠረጠረ ማንኛውም ሰው ልጁ አስቀድሞ ችግር መፍቻ አገልግሎቶች ወይም ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች (ለምሳሌ የአነጋገር፣ የሰውነት ወይም የሥራ ላይ ሕክምናዎች) የማግኘት ብቃቱን ለመገምገም እንዲቻል መጠቆም አለበት ።

የምርመራና የግምገማ ጥቆማዎች ለማንኛውም አሁን ሜሪላንድ ውስጥ ለሚኖር ልጅ፣ ልጁ የግል ወይም የመንግሥት ትምህርት ቤት ቢሄድም፣ ቤት ውስጥ የሚማር ቢሆንም፣ ቤት አልባ ቢሆንም፣ ሽግግር ላይ ያለ ቢሆንም ወይም በስቴቱ ኃላፊነት የሚያድግ ልጅ ቢሆንም ለሁሉም ይሆናል። ማለፊያ ውጤት ለሚያገኙና ከደረጃ ወደ ደረጃ በማለፍ ላይ ያሉ ልጆችም አገልግሎቶች ለማግኘት ብቃት ሊኖራቸው ይችላል።

## አንድ ልጅ የእድገት መዘግየት ወይም የአካል ጉዳት አለበት ብለው ከጠረጠሩ ይደውሉልን!

ለልጁ ዕድሜና ለሚኖርበት አውራጃ ተገቢ በሆነው መጠቆሚያ ስልክ ቁጥር ይደውሉ። (የመጠቆሚያ ስልክ ቁጥሮች ፊት ለፊት ያለው ገጽ ላይ ተጠቅሰዋል።) እርዳታ ለማግኘት ወይም በይበልጥ መረጃ ለማግኘት፣ የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ የልዩ ትምህርት/አስቀድሞ ችግር መፍቻ አገልግሎቶች ጋር በነጻ በስልክ ቁጥር 1-800-535-0182 ይደውሉ።

## በሜሪላንድ ውስጥ የአካባቢው መጠቆሚያ ቁጥሮች

| የአካባቢው አውራጃ | ዕድሜያቸው እስከ 3 ዓመት ለሆኑ<br>የሜሪላንድ ሕጻናትና ልጆች መርሃ ግብር “አንድ ጊዜ መግቢያ” | ዕድሜያቸው ከ 3ዓመት እስከ 21 ዓመት ለሆኑ<br>በሜሪላንድ ውስጥ የአካባቢው የትምህርት ቤት ሥርዓቶች “ልጅ ማግኛ” |
|---|---|---|
| Allegany አውራጃ | 301-689-0466 | 301-759-2082 |
| Anne Arundel አውራጃ | 410-222-6911 | 410-766-6662 |
| Baltimore City | 410-396-1666 | 443-984-1011 |
| Baltimore አውራጃ | 410-887-2169 | 410-887-3017 |
| Calvert አውራጃ | 410-414-7034 | 410-535-7388 |
| Caroline አውራጃ | 410-479-3246 | 410-479-3246 |
| Carroll አውራጃ | 410-876-4437 ext. 277 | 410-751-3295 ወይም 410-751-3033 |
| Cecil አውራጃ | 410-996-5444 | 410-996-5444 |
| Charles አውራጃ | 301-609-6808 | 301-753-1745 |
| Dorchester አውራጃ | 410-221-1111 ext. 1023 | 410-221-1111 ext. 1023 |
| Frederick አውራጃ | 301-600-1612 | 301-644-5292 ወይም 301-644-5276 |
| Garrett አውራጃ | 301-334-1189 | 301-334-7655 |
| Harford አውራጃ | 410-638-3823 | 410-638-4386 ወይም 410-638-4387 |
| Howard አውራጃ | 410-313-7017 | 410-313-7046 |
| Kent አውራጃ | 410-778-7164 | 410-778-7164 |
| Montgomery አውራጃ | 240-777-3997 | 301-947-6050 |
| የ Prince George አውራጃ | 1-800-469-1865 | 301-808-2719 ወይም 301-817-3147 |
| የQueen Anne አውራጃ | 410-758-0720 ext. 4456 | 410-758-2403 ext. 182 |
| Somerset አውራጃ | 410-623-2037 | 410-651-1616 |
| የSt. Mary አውራጃ | 301-475-4393 | 301-475-5511 ext. 213 |
| የSt. Mary አውራጃ | 410-820-0319 | 410-820-8263 |
| Washington አውራጃ | 301-766-8217 | 301-766-2964 |
| Wicomico አውራጃ | 410-677-5250 | 410-677-5250 |
| Worcester አውራጃ | 410-632-5033 | 410-632-5033 |

የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ
የልዩ ትምህርት ክፍል/አስቀድሞ ችግር መፍቻ አገልግሎቶች
የነጻ ስልክ 1-800-535-0182